
# እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20/2018 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ወደ ሀገራች እየገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር ከዕለት ወደ ዕለት ከመጠናከሩ ጋር ተያይዞ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን ተስፋፍቶ ተስተዉሏል፡፡ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንዲኖር መንስዔ ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎችም ላይም ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎችም ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ የምዕራብ ኦሮሚያ፣ ምስራቅ አማራ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ትግራይ፣ የደቡብ ህዝቦች እና ምስራቅ አካባቢዎች ላይም ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስ ያህልም በማንኩሽ 91.2፣ በቡርጂ 74.4፣ በሀረር 39.1፣ በአብኣላ 30.1፣ በደብረታቦር 32.0፣ በጂንካ 39.7 እና 32.1፣ በሊሙገነት 34.1፣ በማጨዉ 37.5፣ በሚሌ 52.4፣ በማፀምሪ 34.8፣ በሳዉላ 31.0፣ በቋራ 46.8፣ በአዲስ አበባ 38.8፣ በአምቦ 36.1 እና 32.1፣ በጨፋ 30.2፣ በሆሳና 35.2፣ በጅማ 39.5፣ በኢጃጂ 45.4፣ በባቲ 30.7፣ በቻግኒ 30.8፣ በዲላ፣ 37.8፣ በእነዋሪ 45.4፣ በነቀምቴ 33.4፣ በበደሌ 34.3፣ በሻምቡ 41.9፣ በአቦቦ 36.1፣ በአድዋ 58.4፣ በአርጆ 32.2 እና በአይራ 40.7 በሚሜ ይገኙበታል::


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም የአማራ፤ የትግራይ፤ የጋምቤላ፤ የቤንሻጉል ጉሙዝ፤ የምዕራብ ኦሮሚያ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ከሞላ ጎደል ሁሉም ዞኖች፤ የፋፈን፣ የአርሲ፣ የምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ የጉጂ እና ቦረና ዞኖችን ጨምሮ ከ25-200ሚ.ሜ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ የሸዋ፣ የባሌ፣ የሊበን፣ የአፍዴር፣ የጎዴ እና የኖጎብ ዞኖች ላይም ከ5-23 ሚ.ሜ ከ3 ላነሱ ቀናት ዝናብ አግኝቷል (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር የትግራይ፤ የአማራ፤ የቤንሻጉል-ጉሙዝ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤የጋምቤላ እንዲሁም በምዕራብ እና መካከለኛዉ ኦሮሚያ የሚገኙ ዞኖች፣ የቦረና እና አርሲ ዞኖች፣ የፋፈን የምስራቅና የምዕራብ ሀረርጌ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡


## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



## ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# <u>እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው  ተፅዕኖ</u>

በኦክቶበር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ  በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ ዘግይተዉና ተገልብጠዉ ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰበሎች አዎንታዊ አስተዋፅ የነበረዉ ሲሆን፤ ነገር ግን በአንዳንድ አካባቢዎች የእድገት ጊዜያቸዉን ጨርሰዉ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው ላይ ላሉ የመኸር ሰብሎች አሉታዊ ጎን ነበረዉ፡፡ በሌላ በኩል በምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ  ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት በተለያየ እድገት ደረጃና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታ ነበረዉ። በአንጻሩ ደግሞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ፤ የተገኘዉ እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚካሄድባቸው በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ዘር ለመዝራትና እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደርች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ ነበረው። በተጨማሪም በኣንዳንድ አካባቢዎች የነበረዉ ከባድ ዝናብ በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል ለመጥቀስ ያህል በደብረሲና በጣለዉ ከፍተኛ ዝናብ በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት ማድረሱን መረጃዎች ጠቁመዋል (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4   እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 11-20 በኦክቶብር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና ጥቂት የምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንደነበረባቸው መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በከፊል የምእራብ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ የደቡብ ምስራቅና የሰሜን ምስራቅ ተፋሰሶች ደግሞ መጠነኛ እርጥበት ተስተውሎባቸዋል፡፡ ይህንን ተከትሎ የላይኛው ባሮአኮቦ፣ አብዛኛው አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የገናሌዳዋና የታችኛው ተከዜ ምዕራባዊ አጋማሽ ክፍል ተፋሰሶች ከእርጥበታማ አስከ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል$ በሌላ በከል ጥቂት የላይኛው አባይ፣ መካከለኛውና የታችኛው ተከዜ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ ዋቢሸበሌ፣ አብዛኛው ገናሌ ዳዋ፣ መካከለኛው ባሮ አኮቦና የላይኛው አፋር ደናክል ተፋሰሶች ከከፊል ደረቅ አስከ መጠነኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ተፋሰሶች ናቸው$ የተቀሩት የሰሜን ምስራቅና የደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቃማ ሁኔታ ላይ እንደነበሩ መረጃችን ያመለክታል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 21-31/ 2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በይበልጥ በምዕራብና በደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸውና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በጥቂት የደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ወለጋ፣ አርሲና ባሌ፣ የቦረናና የጉጂ ዞኖች፤ ጋምቤላ፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ የምዕራብ ትግራይ፤ ከአማራ ክልል የሰሜን ጎንደር ዞን፣ ምዕራብ ጎጃም፣ የባህር ዳር ዙሪያ እና አገው አዊ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ፣ የጉራጌ፣ የሲዳማ፣ የጌዲዮ እና የሰገን ህዝቦች እንዲሁም ከሶማሌ ክልል ደጋሀቡር፣ ፊቅ፣ ቀብሪደሃር፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ጎዴ በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ አልፎ አልፎ ከባድ ዝናብ ሊኖር ይችላል፡፡ ከዚህም ሌላ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በአዲስ አበባ፤ በሰሜን ሸዋ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፤ በደቡብ ትግራይ ዞኖች እንዲሁም በምዕራብና በምሥራቅ ሐረርጌ፣ በድሬዳዋ፣ በሐረርና በጅጅጋ እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ከላይ በትንበያዉ እንደተገለጸዉ በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት መደበኛ የዝናብ ወቅታቸው ስለሆነ በእነዚህ አካባቢዎች እርጥበት እንደሚጠበቅ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይኽም ሁኔታ ወቅታዊ ዝናብ ማግኘት በሚጀምሩትና ሰብል አምራች በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በስፋት በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደርች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ እንደሚኖረው ይጠበቃል። በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ የእርጥበት ሁኔታዉ ቀጣይነት የሚኖረው በመሆኑ ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ለመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በአካባቢው ለሚገኙ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች፣ ለመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለግጦሽ ሣር

ልምላሜ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ነገር ግን በአንዳንድ ቦታዎች የሚጠበቀዉ ወቅቱን ያልጠበቀ የእርጥበት ሁኔታ የእድገት ደረጃቸውን ጨርሰው በመድረቅ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች አሉታዊ ጎን ሊኖረው ስለሚችል አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪ አልፎ አልፎ በአዲስ አበባ፤ በሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም በሰሜን ሸዋ፣ በምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ በድሬዳዋ፣ በደቡብ ትግራይ፣ በሐረሪና በጅጅጋ ወቅቱን ያልጠበቀ እርጥበት የሚፈጠርበት ዕድል ሊኖር ስለሚችል ይህም ሁኔታ ዘግይተው ለተዘሩ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች አወንታዊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ አካባቢዎች እድገታቸውን ጨርሰው በመድረቅ እና በመሰብሰብ ላይ ላሉ ሰብሎች አሉታዊ አስተዋጽኦ ሊኖረው ስለሚችል ሰብሉን ከጉዳት ለመከላከል በመሀል በሚገኙት ደረቅ ቀናቶች ሰብሉን መሰብሰብና ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይመከራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሚገኘው እርጥበት በከፍተኛ ቦታዎች ላይ ሊኖር የሚችለውን ውርጭ የመከሰት እድሉን ይቀንሰዋል፡፡

## እ. ኤ. አ ከኦክቶበር 21-31/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ባሉት ጊዜያት ውስጥ በምዕራብና በደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በሚገኙ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠን ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም በደቡባዊው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ ዝናብ ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃችን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ውስጥ የገናሌ ዳዋ፣ ባሮ አኮቦ፣ አብዛኛው ኦሞጊቤና የስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች፣ መካከለኛውና የታችኛው አባይ፣ ተከዜ፣ የላይኛውና መካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ የመካከለኛው ኦጋደን ተፋሰሶች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ በመጠን ከፍ ያለ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ደረቃማ ሁኔታ ላይ እንደሚቆዩ የትንበያ መረጃችን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው የላይኛውና አንዳንድ የታችኛው አዋሽና አንዳንድ የላይኛው የዋቢሸበሌና የኦጋደን ተፋሰሶች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ለኖር ይችላል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ለበጋው ተጠቃሚ ተፋሰሶች የተሻለ የውሃ መጠን እንዲያገኙ የሚረዳ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ተጠቃሚዎች የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተቻለ መጠን በመያዝ ለሚያስፈልገው አገልግሎት እንዲያውሉ ለመጠቆም እንወዳለን፡፡